# Google Meet

**Google Ireland Limited («Google»)**
Gordon House፣ Barrow Street፣ Dublin 4፣ Ireland
https://support.google.com/

*ከዲሴምበር 21፣ 2020 ጀምሮ ተፈጻሚ የሚሆን*

**የውል አጭር መግለጫ**

- ይህ አጭር የውል መግለጫ የአውሮፓ ህብረት ህግ በሚጠይቀው መሰረት የአገልግሎታችንን መሰረታዊ ነገሮች ያብራራል[1]።
- በአገልግሎት አቅርቦቶች መካከል ንፅፅር ለማድረግ እንዲያግዝዎ የታሰበ ነው።
- የአገልግሎት አቅርቦታችንን የተመለከተ ሙሉ መረጃ በሌሎች ሰነዶች ውስጥ ይገኛል።

**አገልግሎቶች**
Google Meet በድር በይነገጽ ወይም መተግበሪያ በኩል በሁሉም መሣሪያዎች እና መሰረተ ስርዓቶች ላይ የቀረበ የቪድዮ ግንኙነት አገልግሎት ነው። በGoogle Meet በኩል ለመገናኘት የበይነመረብ ግንኙነት ያስፈልጋል። በGoogle የቀረበው Google Meet ምክንያታዊ የሆነ ክህሎት እና እንክብካቤን የተጠቀመ ሲሆን፣ ምንም አነስተኛ የአገልግሎት ጥራት ደረጃዎች ያላቸውም አልቀረቡም።

**ዋጋ**
Google Meet ያለምንም ክፍያ የቀረበ ሲሆን፣ አጠቃቀሙም በGoogle የአገልግሎት ውል (በ https://policies.google.com/terms ላይ የሚገኝ) ተገዢ ነው።

**የቆይታ ጊዜ፣ እድሳት እና መቋረጥ**
ከምዝገባ በኋላ ወዲያውኑ Google Meetን ጥቅም ላይ ለማዋል ያገኙታል። Google Meetን ለውሱን የቆይታ ጊዜ የመጠቀም ግዴታ ውስጥ ያልገቡ ሲሆን በማንኛውም ጊዜ እሱን መጠቀም የማቆም ነፃነቱ አለዎት።

**አካል ጉዳት ላለባቸው ዋና ተጠቃሚዎች የሚሆኑ ባህሪያት**
ማያ ገጽ አንባቢን እና የቁልፍ ሰሌዳ አቋራጮችን በGoogle Meet ውስጥ መጠቀም እንዲሁም የተናጋሪውን ሰው መግለጫ ፅሁፎች እንዲታዩ ማድረግ ይችላሉ። ተጨማሪ ዝርዝሮች https://www.google.com/accessibility/ ላይ ይገኛሉ።

**ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች**
<u>የደንበኛ ድጋፍ</u>፦ ስለ Google Meet እገዛ / ድጋፍ https://support.google.com/ ላይ ይገኛል።
<u>ቅሬታዎች</u>፦ አንድን ቅሬታ ቀጥሎ ያለው በሚዘረዝረው አማራጭ የቅራኔ መፍቻ አቅራቢ https://ec.europa.eu/consumers/odr/main/?event=main.adr.show2 ወይም፣ የአገርዎ ህግ በሚጠይቀው መሰረት፣ ሌላ አቅራቢ ጋር ሊወስዱት ይችላሉ። ተጨማሪ ዝርዝሮች በGoogle የአገልግሎት ውሉ ውስጥ ይገኛሉ።
<u>የደህንነት ክስተቶች</u>፦ ያለምንም መዘግየት የደህንነት እና የግላዊነት ክስተቶችን ለማወቅ እንዲሁም ምላሽ ለመስጠት Google ጥብቅ የሆነ የ24/7 የክስተት አስተዳደር ፕሮግራም ይዞ ይቀጥላል። Google የእርስዎን የመስመር ላይ ደህንነት ለማስተዳደር እንዲያግዝዎ የGoogle የደህንነት የማረጋገጫ ዝርዝርም ያቀርባል።
<u>የግል ውሂብ</u>፦ ለGoogle Meet ለመመዝገብ፣ የእርስዎን ስም፣ ኢሜይል እና የስልክ ቁጥር መስጠት አለብዎ። የGoogle የግላዊነት መመሪያ (በ https://policies.google.com/privacyላይ የሚገኘው) Google Meetን በሚጠቀሙ ጊዜ Google በሚሰበስበው የግል ውሂብ ላይ ተጨማሪ መረጃን ያቀርባል። የGoogle የግላዊነት መመሪያ በእርስዎ እና በGoogle መካከል ያለው ውል፣ ወይም የዚህ አጭር መግለጫ አንድ አካል አይደለም።

---

[1] በአውሮፓ ፓርላማ እና የዲሴምበር 11፣ 2018 ምክር ቤቱ አንቀጽ 102(3) መመሪያ (አህ) 2018/1972 የተመሰረተው የአውሮፓ የኤሌክትሮኒክ ኮሙኒኬሽን ደንብ (OJ L 321፣ 17.12.2018፣ ገጽ. 36)።